የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

15 AUG 2023

ቀን/DATE:
ቁጥር/REF NO: የ\143\443/41

ለሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የሚከፈቱ የቅድመ እና ድህረ ምረቃ ኘሮግራሞችን ይመለከታል፡፡</u>

በትምህርት ሴክተር በአጠቃላይና በከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ በተለይ የተጀመረውን የትምህርት ጥራት ስብራት የማከም ሥራዎችን የሚያጠናክሩ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በመተግበር ላይ እንዳለን ይታወቃል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዩኒቨርስቲዎችን በትኩረትና በተልዕኮ የመለየት ጅምር ሥራዎች እየሰራን መቆየታችን ይታወሳል። በዚህ የሪፎርም ሥራ ዩኒቨርስቲዎች ባላቸው የሰውና የቁስ ሃብት፣ ልምድና ተሞክሮዎች እንደዚሁም ያለበትን የኢኮኖሚ ኮሪደር ከግንዛቤ በማስገባት የትምህርት ኘሮግራሞችን የመከለስ (የማስፋትና የማጥበብ) ተግባር እንዲፈጽሙ ይጠበቃል፡፡ በ2016 የእቅድ ዘመን በመሰጠት ላይ ያሉ የቅድመና ድህረ ምረቃ ኘሮግራሞች በዝርዝር ተፈትሸውና ተገምግመው ከዩኒቨርስቲዎች ልየታ ጋር መጣጣማቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፡፡

ስለሆነም የትምህርት ፕሮግራም ተገምግመው ከዩኒቨርስቲዎቻችሁ ተልዕኮና ትኩረት ጋር መጣጣማቸውን እስኪረጋገጥ ድረስ አዳዲስ ኘሮግራሞች የመክፈት ሥራ መግታት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የታቀዱ አዳዲስ ፕሮግራሞች ለመክፈት የሚደረጉ ጥናቶች ባሉበት እንዲቆዩ እንደዚሁም በቦርድ የፀደቁና በትምህርት ሚኒስቴር የተመዘገቡ አዳዲስ ኘሮግራሞች ተማሪ መቀበል እንዳይጀምሩ እያሳሰብኩ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢዎች በጥብቅ እንዲመሩት የዚህ ደብዳቤ በግልባጭ የተመዘገበላቸው መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ</u>፡-
ለክቡራን ሁሉም የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢዎች
<u>ባሉበት</u>
ለሚኒስትር ጽ/ቤት
ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት [ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ]
<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>

<u>እንዲያውቁት</u>
ለኢ.ፌዲሪ ኘላንና ልማት ሚኒስቴር
ለኢ.ፌዲሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

CamScanner